# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

*ፕሮግራም፡ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 13 ሜትር ባንድ*

*Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on n25 meter band*

ታህሳስ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.
Dec 28. 2011

### ለፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ የሬዲዮ ስርጭት ወዳጆችና ደጋፊዎች ሁሉ !!

ፍኖተ ዴሞክራሲ የሬዲዮ ስርጭት ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ያለማቋረጥ በወዳጆቹና ደግፊዎቹ ድጋፍና ትብብር "ሕዝብ የማወቅ መብት አለው" የሚለውን መሰረታዊ የሰብአዊ መብት መርህ ተግባራዊ እንዲሆን የተቻለውን ሁሉ አድርጓል፡ አሁንም እያደረገ ይገኛል። የፍኖተ ዴሞክራሲ የዜና አቅርቦት፡ ወቅታዊና ዋና ዋና በሆኑ ሀገራዊና ሀገራዊ ነክ በሆኑ አለም አቀፋዊ የፖለቲካ፡ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ርዕሶች ላይ የሚደረጉ ትችቶች፡ ጥናታዊ ትንተናዎች፡ ቃለ መጠይቆች፡ የተለያዩ ንባባዊ መግለጫዎች፡ ግንዛቤ ሊያዳብሩ የሚችሉ የትግል ተመክሮዎች አይነተኛ መለያዎቹ ናቸው። ይህንንም ገለፃ እንዲሰጥ በተጋበዘበት ሕዝባዊ መድረኮች ሁሉ ማብራሪያዎችን ለአድማጮቹ ሰጥቷል። በተናጠል ለተገናኛቸው ግለሰቦች ደግሞ እንደሁኔታው የፍኖተን ራዕይና ተግባር አስተዋውቋል። በደብዳቤ አምዳችን ከአድማጮቻችን የሚቀርቡልን አስተያየቶች የዚሁ ጥረታችን ውጤቶች ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም።

መድበላዊ ሥርአት እንዲገነባ፡ የፖለቲካ አመለካከት እንዲሰፋና ግልፅነት እንዲኖር፡ በተለያዩ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ ሕዝባችን የራሱንም ሆነ የሀገሩን የወደፊት እጣ ለመወሰን እንዲችል ለማድረግ እንደ ፍኖተ ዴሞክራሲ የመሰሉ የሬዲዮ ስርጭቶች በአማራጭነት በመድረኩ በቀጣይነት መኖር ምን ያህል ወሳኝነት እንዳለው ለሕዝብ ቀናኢ ለሆኑ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ግልፅ ነው። የመለስ አገዛዝ ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ከሕዝባችን ጋር የገባው ቅራኔ እየተባባሰ በመምጣቱ እጅግ አስቸጋሪ፡ አስከፊና አሳፋሪ የመብት ጥሰቶችና አፈናዎች በሕዝባችን ላይ እያካሄደ ይገኛል። የመፃፍ፡ የመናገር፡ ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት በተግድቧል ቁንጽል ቃላት የሚገለፅ ሳይሆን ጨርሶውኑ የሌለ ነው። ዴሞክራሲያዊ ሥርአት ያለነዚህ መብቶች ያለምንም ገደብ መከበር እንደማይመሰረት ደግሞ ቢያንስ ያለፉት 20 አመታት ከምጊዜውም በበለጠ ግልፅ ያደረጉት ነው።

በመለስ አገዛዝ አምባገነናዊ ሥርአት ዴሞክራሲና ሰብ አዊ መብቶች ሕዝቡ እንዲገለገልባቸው ሳይሆን ውስታዊ ይዞታቸውን እንዳሻ በመተርጎም ለአገዛዙ ማጠናከሪያና ሕዝብን ለማፈን መጠቀሚያ በተደረጉበት ተጠያቂነቱና አገልግሎቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሆነ የዜና ስርጭት ተቋም በቀታይነት መኖር ጠቃሚነቱን ከሕዝባችንና ቀና ወዳጆቹ የበለጠ የሚያውቅ የለም። በሀገሩ ስለሚገኘው ፖለቲካዊ፡ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁናቴ ከተለያየ አቅጣጫ ጠንቅቆ ለማወቅ እንዲችል መድረኩ የተመቻቸለት ሕዝብ ከሚቀርቡለት የተለያዩ አማራጮች፡ ፍላጎቱንና ጥቅሙን በምን አይነት ለማስጠበቅ የሚያስችለው ውሳኔ ለመውሰድ የሚቸገር አይሆንም። የፍኖተ ዴሞክራሲ ተደማጭነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድ ለዚህ ሁናቴ በቂ ምስክር ነው። ከዚህ በበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም እናምናለን።


Telephone 202- 291- 4217 Fax. 202-291-7645
www.finote.org email: efdpu@aol.com

በመሆኑም በመለስ አገዛዝ የሚካሄዱ የሕዝብን መብት የሚጥሱ፥ ሀገርንና ብሔራዊ ጥቅምን የሚጎዱ ተግባሮች፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት እንዳይመሰረት የሚያደርጉ ማናቸውንም ሕጎች፥ ደንቦች፥ እንቅስቃሰዎች፥ በዝርዝር በመተንተንና በማቅረብ እናጋልጣለን። ሳምንታዊ የዜና ዘገባም ሆነ ከዝግጅት ክፍላችን በዚሁ ላይ ያተኮሩ ናቸው። በሌሎች መሰል ፀረ ኢትዮጵያ ቡድኖች የሚታሰቡ ሀገርንና ሕዝብን የሚጎዱ እንቅስቃሴዎችንም ፈልፍሎና አቀናብሮ ለሕዝብ ማሳወቁንና የመቋቋሚያ መፍትሄዎችንም መጠቆሙን አቅማችን በፈቀደ መጠን እንቀጥልበታለን።

ትግላችን አቤቱታ ለመለስ አገዛዝ ማቅረብና ሩህሩህነቱን መጠበቅ ሳይሆን ከመሰረተው ሥርአት ጋር እንዲወገድ መታገል ነው። የዜጎችን እኩልነት የሚፃረሩ፤ የሀገር ሉአላዊነትን የሚሸረሽሩ፥ ብሔራዊ ጥቅምን ለባዕድ የሚሸጡ፥ ሀገሪቷ ያላትን እምቅ ሀብት ብዙሃኑ ተቋዳሽ እንዳይሆን መሰናክል የሚፈጥሩ፥ ብሔራዊ መግባባት እንዳይኖርና ክፍፍል እንዲነግሥ የሚፈልጉትን ሁሉ የሚወገዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይቻል ዘንድ ፍኖተ ዴሞክራሲ ከሕዝብ ጎን በመሆን የበኩሉን አስተዋፅዖ ለማበርከት በጥረት ላይ ይገኛል። ይህ ተሟልቶ ሊገኝ የሚችለው ግን በሀገር ወዳዱ ሙሉ ድጋፍና እርዳታ ለሁላችሁም ግልፅ ነው። በመሆኑም እርዳታችሁን በሚከተለው አድራሻ አመቺ መስሎ በታያችሁ መንገድ ልትልኩልን ትችላላችሁ።

| | |
|---|---|
| አድራሻችን | Finote Democracy<br>P.O.Box 73337<br>Washington DC 20056, USA |
| የባንክ አድራሻ | Kölner Bank eG<br>Account Nr. 451 275 003<br>Code (BLZ) 371 600 87<br>Hohenzollernring 31- 35<br>50762 Köln<br>Germany |

ከጀርመን ውጭ ለምትኖሩና ምናልባት ከባንክ ሰራተኞች በኩል አለም አቀፍ ቁጥሩን የምትጠየቁ ከሆነ እንደሚከተለው ማሳወቅ ትችላላችሁ።

BIC G E N O D E D 1 C G N
IBAN DE47 3716 0087 045 1275 003

ወደፊት ለምናደርገው የዜና ስርጭትና ትንተና የናንተ ቅንና ገንቢ የሆነ ትችት እንደማይለየን ተስፋችን የጎላ መሆኑን እየገለፅን ከዚህ ቀደም ላደረጋችሁልንና ወደፊትም ለምታደርጉሉን እርዳታ ከወዲሁ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

የፍኖተ ዴሞክራሲ የሬዲዩ ስርጭት
አዘጋጅ ክፍል